# ፖሊሲ

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

***ተዛማጅ ደንቦችና መመሪያዎች፡-*** ABA, ABC-RA, ACA, ACG, BFA, BMA, FAA, IEA, IEB, IED, IFB, IGK, IGP-RA, IRB-RA, KBA, KBA-RA, KLA, KLA-RA

***ኃላፊነት የሚመለከታቸው ጽ/ቤቶች፡-*** *ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት፡-* Office of Communications; Office of School Support and Well-being; Office of Well-being, Learning, and Achievement

## ቤተሰብ-ትምህርት ቤት አጋርነቶች

**A. ዓላማ**

1. ተማሪዎቻቸውን እና የተማሪዎቻቸውን ትምህርት ቤቶች በሚመለከቱ ጉዳዮች የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ የወላጆችን/የአሳዳጊዎችን ተሳትፎና ሚና ለማዳበር አካታች፣ ባህላዊ፣ ምላሽ ሰጪ፣ እና ከዘረኝነት ነፃ የሆነ አሠራር [1] ለመመስረት።
2. ከብሔራዊ የቤተሰብ እና የትምህርት ቤት አጋርነት መስፈርቶች ጋር በማጣለጥ እና የፌዴራል መስፈርቶችን ድንጋጌ በመቃኘት ረገድ የቤተሰብ እና የትምህርት ቤት አጋርነትን መርህ ለማረጋገጥ
3. የሰራተኞች፣ የወላጆችን/የአሳዳጊዎችን/የቤተሰቦችን አቅም በመገንባት የሁሉንም ልጆች ትምህርት እና ደህንነት በመደገፍ ትርጉም ያለው የሁለት ወገን አጋርነት ላይ እንዲሳተፉ ለማበረታታት

**B. ጉዳዩ**

ቤተሰቦች የልጆች የመጀመሪያ አስተማሪዎች ናቸው፣ ስለሆነም ተማሪዎች ለትምህርት እድሜ ሲደርሱ፣ጤናማ፣ ጠንካራ፣ መሥራት የሚችሉ ብቁ ወጣት ጎልማሶች ሆነው እንዲያድጉ ለመንከባከብ የጋራ ግብ ላይ በመመሥረት ቤተሰቦች እና የትምህርት ቤት ሰራተኞች የመተጋገዝና አጋር የመሆን እድል አላቸው።

**C. አቋም**

1. ቦርዱ ሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ(MCPS) ሰራተኞች ከተማሪዎች ቤተሰቦች ጋር በመተባበር ከሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ ስኬት የሚጠበቅ መሆኑን እንዲያስገነዝቡ እና እንዲያረጋግጡላቸው ይጠብቃል።

2. ለተማሪ ስኬት ጠንካራ የቤተሰብ ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑን ቦርዱ ያምናል። ጠንካራ የቤተሰብ ተሳትፎ አቀራረብ የሚያረጋግጠው –

    a) ሁሉም ወላጆች/አሳዳጊዎች ለተማሪዎቻቸው ያላቸው ህልም ለልጆቻቸው ጥሩ እንዲሆንላቸው

---

[1] በዚህ ፖሊሲ ዓላማ መሠረት “ወላጅ/አሳዳጊ” እና “ቤተሰብ” የተባሉት ቃላት ሳይለዋወጡ በሚከተሉት ሁኔታዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡- "ወላጅ/አሳዳጊ" የሚለው ቃል ልጅን ወክሎ ትምህርታዊ ውሳኔዎችን ለማድረግ ህጋዊ ኃላፊነት ያለውን ሰው ይገልጻል፣ "ቤተሰብ" የሚለው ቃል የሚገልፀው ከተማሪ ህጋዊ ሞግዚትነት በተጨማሪ ልጆችን እና የትምህርት ቤት ማህበረሰብን ወክለው በርካታ ጉዳዮችን የሚያከናውኑ የቤተሰብ አባላትን ሚና ለመግለጽ ነው።

ይፈልጋሉ፣

b) ሁሉም ወላጆች/አሳዳጊዎች ለተማሪዎቻቸው በት/ቤት እና በማህበረሰባቸው ውስጥ ስላሉት መገልገያ ሀብቶች/ሪሶርሶች እና እድሎች በመገንዘብ የተማሪዎቻቸውን ትምህርት የመደገፍ አቅም አላቸው።

c) በት/ቤት እና በቤት መካከል አጋርነትና ትብብር እንዲጎለብት የማድረግ ሃላፊነት በዋናነት የትምህርት ቤት ሰራተኞች ሚና ሲሆን፣ በተለይም የት/ቤት መሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች እና የትምህርት ቤት ሰራተኞች በሙሉ ለተማሪዎች የላቀ ውጤት ቁርጠኛ መሆናቸውን እንዲተማመኑ የሚያበረታቱ እና የተማሪዎችን ስኬት ለማበረታታት ሁሉም ወገን እኩል አጋሮች መሆናቸውን ማረጋገጥ ይችላሉ።

d) በትምህርት ቤት ማህበረሰብ ውስጥ ባሉ ቤተሰቦች መካከል የሚከናወኑ ጉልህና ትርጉም ያላቸው ግንኙነቶች እና ማህበራዊ አውታረ መረቦች ጠንካራ የትምህርት ቤት-ቤተሰብ ግንኙነቶችን ለማጎልበት ይረዳሉ።

3. በብሔራዊ የወላጆች እና የመምህራን ሕብረት *ብሄራዊ የቤተሰብ እና የት/ቤት አጋርነት መመሪያ* ላይ በመመስረት ቦርዱ ለተማሪዎች ስኬት ጠቃሚ ስለሆነ የቤተሰብ እና የትምህርት ቤት ትብብርና አጋርነት የሚከተሉትን ስድስት መርሆች አስቀምጧል።

a) *ቤተሰቦችን ሁሉ በመልካም ሁኔታ መቀበል፡-*

*ፖሊሲ* ACA፥ *አድሎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት እና ባህላዊ ብቃት* ላይ እንደተገለጸው ቦርዱ ሁሉም ወላጆች/አሳዳጊዎች በልጆቻቸው ትምህርት ጉዳይ ያላቸውን ተሳትፎ ለማበረታታት ግምታዊ ወይም ትክክለኛ የግል ባህሪያት ላይ ተንተርሶ የሚነሳውን የተዛባ አመለካከት በማረም ንቁ ተሳትፏቸውን የሚያደናቅፉ እንቅፋቶችን ለማስወገድ ይሰራል።[2] MCPS እና የአካባቢ ትምህርት ቤቶች ምቹ፣ ምላሽ ሰጪ እና አካታች የትምህርት አውድ ይፈጥራሉ፣ ይኸውም –

(1) ቤተሰቦች እና ተማሪዎች ተሰሚነት እንዳላቸው እና እንደሚከበሩ እና ከህብረተሰቡ ጋር ባላቸው መስተጋብር የባለቤትነትና የግንኙነት ስሜት እና ምቾት እንዲሰማቸው ማድረግ፤

(2) የቤተሰብ ተሳትፎ ተግባራት የተማሪዎቻቸውን አካዴሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ እድገትን የሚደግፉ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ተዛማጅ መረጃዎችን ለማግኘት እንዲችሉ የቤተሰቦችን ፍላጎት ለማሟላት ሆን ተብሎ የተነደፉ ናቸው።

(3) የትምህርት ቤት ማህበረሰቦች የሁሉንም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ማህበረሰቦች የተለያዩ ወጎች፣ ማንነቶች፣ እና ልምዶችን የሚገነዘቡ ናቸው።

b) *ውጤታማ መስተጋብር/ግንኙነት ማድረግ፡-*

ለቤተሰቦች ቀደምት እና ጥልቅ ግንዛቤን ለማስጨበጥ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እና የአካባቢ ትምህርት ቤት ሰራተኞች እና ቤተሰቦች ስለ ተማሪዎች ትምህርት እና

[2]የግል ባህሪያት፡- ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ የዘር ሐረግ፣ ብሔር፣ ዜግነት፣ ሃይማኖት፣ የስደት ሁኔታ፣ ጾታ፣ የፆታ ማንነት፣ የፆታ መገለጫ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የቤተሰብ መዋቅር/የወላጅ ሁኔታ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ዕድሜን ጭምር ያካትታል። ችሎታ (የአእምሮ ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግስት ጥበቃ የሚደረግላቸው ባህሪያትን ወይም ግንኙነቶችን ሁሉ ይመለከታል።

እድገት በርካታ፣በስልት በሚተገበሩ መንገዶች እና መሣሪያዎች ትርጉም ባለው የሁለትዮሽ ግንኙነት ይሳተፋሉ።

(1) የሁለት-ወገን የመገናኛ ዘዴዎች እና ሂደቶች ወላጆች/አሳዳጊዎች ከአካባቢያቸው ትምህርት ቤቶች ጋር እንዲገናኙ እና ተማሪያቸው በትምህርት ቤት ስላለው/ስላላት ስኬት እና ደህንነት መረጃ የመጠየቅ እድል እንዳላቸው እንዲገነዘቡ ማበረታታት አለባቸው።

(2) በፌዴራል *እያንዳንዱ ተማሪ ስኬታማ ይሆናል ህግ* ድንጋጌ *መሠረት፤* ስለተማሪዎቻቸው ድጋፍ መስጠት እና ማቀንቀን ለሚፈልጉ ወላጆች/አሳዳጊዎች የማስተርጎም ወይም የጽሑፍ ትርጉም አገልግሎት መስጠት፣ስብሰባዎችን ማመቻቸት ወይም ሌላ የተሻለ የግንኙነት መረብ አማራጮችን መዘርጋት እንደሚያስፈልግ ቦርዱ በመደበኛነት የሚገነዘበው ጉዳይ ነው።

(3) ዉጤታማ፣ አካታች፣ ባህላዊ ምላሽ የሚሰጥ፣ እና ከዘረኝነት ነጻ የሆነ የመግባባት/የኮሙኒኬሽን ስልት፡- ሁሉም ቤተሰቦች ወሳኝ ትምህርታዊ መመዘኛዎችን፣ የኮርስ ቅደም ተከተሎችን፣የተማሪ አገልግሎት-ትምህርት መስፈርቶችን እና እድሎችን፣ የማግኘት ተደራሽነት ይኖራቸዋል። ተማሪዎቻቸው ጠንካራ ትምህርት የመማር እድሎችን (ለምሳሌ፡- ማግኔት፣ ከፍተኛ ተሰጥኦ እና ችሎታ ያላቸው፣ የቋንቋ ኢመርዥን፣ እና ጥምር የምዝገባ ፕሮግራሞች፣ ለኮሌጅ እና ለስራ ዝግጁነት የሚያበቁ ኮርሶች፣ ኢንዱስትሪን ጨምሮ የተማሪዎቻቸው የመተግበሪያዎች አጠቃቀም፣ እና የታወቁ የሙያ ሠርተፊኬቶች እና ሌሎች የሙያ ማረጋገጫ፣ ስኮላርሺፕ፣ እና የአመራር-ብቃትን የማዳበር  እድሎችን ያጠቃልላል)።

(4) ከቦርድ ፖሊሲ KBA አንጻር፣ *የህዝብ መረጃ ተደራሽነት ፖሊሲ፣* ጋር ተስማሚ በሆነ መልኩ ቦርዱ ለሰፊው ማህበረሰብ የተቻለውን ያህል የመረጃ ተደራሽነትን ያበረታታል።

c) *የተማሪዎችን ስኬት መደገፍ፡-*

(1) ቤተሰቦች የልጆቻቸውን ትምህርት ለመደገፍ የሚያስችላቸው ውጤታማ፣ ሁሉን አቀፍ፣ ባህላዊ፣ እና የቋንቋ ብቃትን የሚያዳብር የቤተሰብ ተሳትፎን ለማሳደግ እንዲችሉ የሰራተኞችን የግንዛቤ አቅም ለመገንባት ቦርዱ ቁርጠኛ ነው።

(2) የተማሪዎችን የትምህርት ጉዳይ በሚመለከቱ ውሳኔዎች ላይ በትምህርት ቤትና - የተማሪዎች ቤተሰብ መካከል የሚደረግ ግንኙነት/ኮሙኒኬሽን እና በት/ቤት እና የማህበረሰብ ህይወት ላይ ትርጉም ያለው የቤተሰብ ተሳትፎን በሚመለከት የተለያዩ ቡድኖችን የማያካትቱ ልማዳዊ አሠራሮችን ለመለየት እና አማራጮችን ለማዘጋጀት ከዚህ ቀደም ሲሠራባቸው የነበሩ የተለመዱ አሰራሮች በጥልቀት መፈተሽ  አለባቸው።

(3) የተሳትፎ ሁኔታዎች በትኩረት ሲመረመሩ፥ የቦርድ አባላት እና ሰራተኞች የወላጅ/አሳዳጊ የስራ መርሃ ግብሮችን እና የተለያዩ የጊዜ እና የተሳትፎ አማራጮችን ግምት ውስጥ ያስገባሉ።

---

[3] ስለ እያንዳንዱ ተማሪ ስኬታማነት የፌዴራል ህግ (ESSA፤ 2015) ታይትል I፣ ታይትል III እና ታይትል IV ፕሮግራሞች፡ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው እና በስደተኛነት የመጡ ተማሪዎች እና ጀማሪ የቋንቋ ተማሪዎች የመሣሰሉትን፣ የተማሪዎች አካዳሚያዊ ትምህርት በሚመለከት ትርጉም ያለው መደበኛ፣የሁለት ወገን ግንኙነት እንዲሳተፉ የወላጆች/አሳዳጊዎች/ቤተሰቦች እና የትምህርት ቤት ሰራተኞችን ግንኙነት ለማዳበር አስፈላጊ ነገሮችን መገንባት እንደሚገባ ይደነግጋል።

d) *ስለ እያንዳንዱ ልጅ ማሰብና መቆም መናገር ያስፈልጋል፡-*

MCPS እና የአካባቢ ትምህርት ቤቶች ሰራተኞች የቤተሰቦችን፣ የተማሪዎችን እና ሰራተኞችን በቤተሰብ ተሳትፎ ላይ ያለውን አድልዎ እንዲገነዘቡ እና እንዲያስወግዱ እና ፍትሃዊ አሠራር እና ፍትሃዊ ተደራሽነት እንዲኖር ለሁሉም ተማሪዎች እድል እንዲኖሯቸው ድጋፍ በመስጠት ያበረታታሉ

e) *ኃላፊነትና ሥልጣንን ማጋራት*

(1) ቤተሰቦች እና የትምህርት ቤት ሰራተኞች በልጆች ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ውሳኔዎችን በተመለከተ የተለየ መረጃ ያላቸው አስፈላጊ እና ዋጋ ያላቸው አጋሮች ናቸው። የትምህርት ቤት ሰራተኞች የተሳትፎ ግቦችን ለማሳካት ተስማሚ የሆኑ ዘዴዎችን በመጠቀም የትምህርት ቤት ህጎችን፣ ልምዶችን እና ፕሮግራሞችን ለመፍጠር ከቤተሰቦች እና ከተማሪዎች ጋር ይመካከራሉ፥ ይተባበራሉ።

(2) በቦርድ ፖሊሲ ABA፣ *የማህበረሰብ ተሳትፎ* ላይ እንደተገለጸው፣ ት/ቤቶች በትምህርት ቤቶች ማሻሻያ እቅድ እና አዲስ ነገር የመለወጥ ሂደቶች ላይ እንዲሁም በቦርድ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የትምህርት ቤት ማህበረሰብን የሚወክሉ የወላጆች/አሳዳጊዎችን ተሳትፎ በጥብቅ ይፈልጋሉ።

f) *ከማህበረሰብ ጋር መተባበር፡-*

(1) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እና የአካባቢ ትምህርት ቤት ሰራተኞች የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማጎልበት በተማሪዎች የሚመሩ ድርጅቶችን፣ የተማሪዎች አመራር እና የተማሪዎችን ዝንባሌና ፍላጎት የሚያቀነቅኑ ቡድኖችን በማነቃቃት የተማሪዎች አካዳሚያዊ ፍላጎቶች እና እድገታቸውን ያበረታታሉ። MCPS እና የአካባቢ ትምህርት ቤቶች ትምህርት ቤቶችን የሚመለከቱ ውሳኔዎች ላይ ከተማሪ መሪዎች እና ከመሳሰሉ ድርጅቶች አባላት ጋር ከፍላጎታቸው ጋር በማዛለጥ ለሚያደርጉት የተሳትፎ ግቦች ተስማሚ ዘዴዎችን በመጠቀም ይሳተፋሉ/ያሳትፋሉ።

(2) MCPS እና የአካባቢ ት/ቤት ሰራተኞች በተማሪዎችና ቤተሰቦች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገነቡትን የበርካታ ድርጅቶች ድጋፍ እና ለተማሪዎች እድገት፣እንዲሁም ስለልጆቻቸው ትምህርትና ስኬት ደጋፊ የሆኑ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ለት/ቤት ማህበረሰብ ያላቸውን ጠቃሚ አስተዋፅዖ ዋጋ በመስጠት እውቅና ይሰጣሉ። ቦርዱ ለተማሪዎች ፍትሃዊ ተሞክሮዎችን ለመስጠት የተቻለውን ሁሉ ጥረት ማድረግ ይፈልጋል። MCPS እና የአካባቢ ትምህርት ቤቶች ከእንደዚህ አይነት ድርጅቶች መሪዎች እና አባላት ጋር ከት/ቤት ጋር በተያያዙ ትኩረት በሚሰጥባቸው ጉዳዮች ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ላይ ይሳተፋሉ ከተሳትፎ ግቦች ጋር የሚስማሙ ዘዴዎችን በመጠቀም።

(3) MCPS እና የአካባቢ ትምህርት ቤት ሰራተኞች ከማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ተማሪዎችን ከተማሪ አገልግሎት ትምህርት እና የሙያ ዝግጁነት እድሎች ጋር ለማገናኘት ይተባበራሉ።እንዲሁም ቤተሰቦችን እና ሰራተኞችን ከማህበረሰብ አገልግሎት ጋር ለማገናኘት ተግተው ይሠራሉ።

D. **ተፈላጊው ውጤት**

ሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ጤናማ፣ ጠንካራ እና ብቁ ወጣት ጎልማሶችን እድገት የመንከባከብ የጋራ ግብ ለማሣካት፥ ጠንካራ የቤተሰብና የትምህርት ቤት ትብብርን ለመገንባት ከሁሉም ቤተሰቦች ጋር በመተባበር ውጤታማ ሥራ ይሰራሉ።

E. **የአተገባበር ስልቶች**

1. የትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት የተማሪዎችን ትምህርት በሚመለከቱ ጉዳዮች የቤተሰብና የትምህርት ቤት ትብብር ውጤታማ፣አካታች፣ባህላዊ አግባብነት ያለው እና ከዘረኝነት ነጻ በሆነ ዘይቤ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን እንደሚከተለው በአጋርነትና በእኩልነት ያሳትፋሉ፡-

   a) ደንቦችን እና አሰራሮችን በማዳበር እና በመተግበር (በዚህ ብቻ አይወሰንም) የሚያካትተውም –

      (1) ቤተሰቦች የተማሪዎቻቸውን የትምህርት ፕሮግራም ማግኘትና ማወቅ እንዲችሉ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ትርጉም ተደራሽ ማድረግ፣ ይሄውም ከፌደራል እና ከስቴት ህግ ጋር ተስማሚ በሆነ መልኩ ነው፤ እና

      (2) የቋንቋ ማስተርጎም እና የጽሑፍ ትርጉም አገልግሎቶችን መስጠት።

   b) ውጤታማ እና ሁሉን አቀፍ የቤተሰብ ተሳትፎ ግቦችን መተለም፣ ጠቃሚ መስፈርቶችን እና መመዘኛዎችን ማዘጋጀት፤ በየአመቱ ያሉትን ችግሮች እና የመረጃ ነጥቦችን መከታተል፣ የተሳትፎ መሰናክሎችን ለይቶ ማወቅ፣ በተለይ ወላጆች/አሳዳጊዎች ባልተስተካከለ የግንኙነት ስልት ለተማሪዎቻቸው ስኬታማነት ድጋፍ መስጠት እንዲችሉ፣ የማስተርጎም ወይም የጽሑፍ ትርጉም ተጨማሪ ድጋፍ ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

   c) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞችን የግንዛቤ አቅም ለማጎልበት እና የተማሪ አካዳሚያዊ ስኬትን እና የት/ቤት አፈጻጸምን ለማሻሻል ውጤታማ የቤተሰብ እና የትምህርት ቤቶችን አጋርነት ለማቀድ እና ለመገንባት አስፈላጊውን ቅንጅት ለማድረግ፣ የቴክኒክ ድጋፍ፣ እና ሌሎች ድጋፎችን የመስጠት ኃላፊነት ያለባቸውን ሰራተኞች ይመድባሉ።

   d) በተቻለ መጠን ትምህርት ቤቶች ስለሚኖራቸው ዝግጅቶች፣ እድሎች እና የግዜ ገደቦች አስፈላጊ መረጃዎችን ለማስተላለፍ ከተማሪዎች ቤተሰቦች ጋር አስተማማኝ ግንኙነቶችን ማከናወን አለባቸው።

   e) ከወላጆች/አሳዳጊዎች እና ቤተሰቦች ጋር ይማከራሉ፣ ለተሳትፎ ግቦች ተስማሚ የሆኑ ዘዴዎችን በመጠቀምለማዳበር –ይተባበራሉ።

      (1) የቤተሰቦችን ዋጋ ያለው አስተዋፆዎችን መጠቀም፣ እና እንዴት ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር መገናኘት፣ መነጋገር እና መስራት እንደሚቻሉ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለሰራተኞች የሙያ ማዳበር ስልጠና መስጠት፣

      (2) በዓመቱ ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት ለሚመጡ ቤተሰቦች፣ ወይም ስለ MCPS እምብዛም የማያውቁትን ጨምሮ፣ ጠቃሚ እና ውጤታማ የቤተሰብ ተደራሽነት ፕሮግራሞችና ሞዴሎችን/ናሙናዎችን ማዘጋጀት፣

(3) እንግሊዘኛ ከማይናገሩ ቤተሰቦች ጋር የሁለትዮሽ ግንኙነት እንዲዳብር እና ወላጅ/አሳዳጊዎች ስለተማሪዎቻቸው የአካዳሚክ መርሃ ግብሮች በመረጃ ላይ የተመሰረተ ምርጫ እንዲያደርጉ የተዘጋጀ የግንኙነት መዋቅር እና ሌሎች እገዛዎችን ማድረግ፣እና የትምህርት ቤት አክቲቪቲዎች፣ የውሳኔዎችን ቁልፍ አካዴሚያዊ ክንዋኔዎች፣አማራጮችን እና አንድምታዎችን መረዳት፤ እና የመገልገያዎችን/ሪሶርሶችን ተደራሽነት ማመቻቸት።

f) የሚከተሉትን መረጃዎች ለቤተሰቦች በብቃት የሚያስተላልፉ እና በተቻለ መጠን በሚረዱት ቋንቋ ለትምህርት ቤት አገልግሎት የሚሆኑ አብነቶችን/ሞዴሎችን (templates) እና መሳሪያዎችን ማሰራጨት፡-

(1) የተማሪ አካዴሚያዊ እድገት፣ በትምህርት ላይ መገኘትና ሳያቋርጡ መከታተል፣ እና የት/ቤት ደህንነትን የሚመለከቱ ሌሎች ስጋቶች።

(2) ይህ ፖሊሲ እና የትምህርት ቤት ማሻሻያ ዕቅዶች።

(3) የስቴት የትምህርት ስታንዳርድ፣ የስቴት እና የአካባቢ የትምህርት ምዘናዎች፣ እና የልጆችን ትምህርታዊ እድገት ለመከታተል የሚረዱ መሳሪያዎች።

(4) የተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች፣ የተማሪ የስነምግባር ህጎች (የፍትሃዊ ተሃድሶ ሂደቶችን ጨምሮ)፣ ወሳኝ ትምህርታዊ መመዘኛዎች፣ የአካዳሚክ እቅድ መረጃዎች እና የኮርስ ቅደም ተከተሎች፣ የጊዜ ማእቀፍ እና ለማመልከት የሚያስፈልጉ ሂደቶች፣ ስለ ፈጣን የትምህርት እድሎች (ለምሳሌ፡- ማግኔት፣ ከፍተኛ ተሰጥኦ ያላቸው እና ጎበዝ ተማሪዎች፣ የቋንቋ ኢመርዥን፣ እና ጣምራ የምዝገባ ፕሮግራሞች፣ ለኮሌጅ እና ለስራ ዝግጁነት የሚያበቁ ኮርሶች፣በኢንዱስትሪዎች ተቀባይነት ያላቸው የሙያ ምስክርነቶችን እና ሌሎች ሙያተኞችን ጨምሮ የምስክር ወረቀት፣ ስኮላርሺፕ እና የአመራር ክህሎት እድገት) የመሣሰሉትን እድሎች ይካተታሉ።

(5) ከትምህርት ቤት እና ከወላጅ/አሳዳጊ/ቤተሰብ ፕሮግራሞች ጋር የሚገናኙ ስብሰባዎች እና የወላጆች/አሳዳጊዎች ካውንስል እና ልዩ ልዩ የት/ቤት ዝግጅቶችን የመሳሰሉ ሌሎች ክንውኖች ጋር ተዛማጅ የሆኑ መረጃዎች።

**F.** ***ግምገማ እና ሪፖርት***

ይህ ፖሊሲ የሚገመገመው በትምህርት ቦርድ የፖሊሲ ግምገማ ሂደት ነው።

| | |
|---|---|
| ***ተዛማጅ ምንጮች፡-*** | የእያንዳንዱ ተማሪ ስኬት ህግ (ESSA፤ 2015) ታይትል I፣ ታይትል III እና ታይትል IV" Every Student Succeeds Act (ESSA; 2015) Title I, Title III, and Title IV" |
| ***የፖሊሲው ታሪክ፡-*** | በሥራ ላይ የዋለው ኖቬምበር 13, 1990 በውሳኔ ቁጥር 66990 ነው። ሴፕቴምበር 1996 በውሳኔ ቁጥር 489-02 ተሻሽሏል፣ ኦክቶበር 28 ቀን 2002 በውሳኔ ቁጥር 417-10 ተሻሽሏል፣ ጁላይ 26 ቀን 2010 ተሻሽሏል። |

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን  እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

<table>
<tr><th>በ MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ***</th><th>በ MCPS ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ ***</th></tr>
<tr><td>Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 | SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 | DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator ሰክሽን 504 አስተባባሪ<br>Office of School Support and Well-being<br>Office of Well-being, Learning, and Achievement<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-5630 | 504@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 | DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ***</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 | TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

*ይህ መግለጫ የተሻሻለውን የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።
**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር ይጣለጣል።
***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡- U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, oወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ፌብሩዋሪ 2024